ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ጥር 15 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ሲነገሩ የማይሰሙ፤ ከሀቅ የሚጣሉ፤ ዐይን ከፍተው የሚታወሩ በዙሳ!

ሀገራችን ያልታደለች ሆና ሊሆን ይችላል ተምችና መሓይምነት ያጠቃታል ።ባንዳን አርበኛ ፤ነፍሰ ገዳዩን ነጻ አውጪ፤ቸና ሽ፤መንግስቱ ይመለስልን፤መንግስት አለ፤ ብሔር ነው ገና ያልኖረው (የሹሙ ጥራዝ ነጠቅ ንግግር))፤እኔ አሸጋግራችኋለሁ፤ የኤርትራም የብሄርም ችግር የተከሰተው ከዋለልኝ ጽሁፍ በኋላ ነው፤ ያ ትውልድ ብዙ አትፍቷል የሚሉ ጥራዝ ነጠቅ ትችቶችን በአላዋቂዎች አንደበት ሲለፈፉም መስማት ተገደናል። አውቆ የተኛን ሰው መቀስቀስ ከባድ ነው እንዲሉ አልሰማም ልደናቆርበት ያለንም ለማስተማርና ሲታወር ዓይኑን ለመክፈት በጣም አዳጋች ነው ። አስረጂ ነጋሪ ጠፍቶ አይደለም ። ታሪኩን የማያውቅና ሲነገርም ጆሮን የሚደፍነው በዝቶ ነው ፡፤ስለማያውቁት ጉዳይ አዋቂ መስሎ መናገርን ዛሬ ሹሙም ሳይቀር ልክፍቱ ተጋብቶበት ተያይዞታል ። ሀገር ውዳዶችን፤ ለኢትዮጵያና ለሕዝብ የታገሉትንም መወንጀልና መክሰሰ፤ማውገዝ ሰፍኖ በአንጻሩ ሀገር ያጠፉትን ማወደስ ማሞገስን የመረጡ ጥቂቶች አይደሉም ። ስንቱን ንጹህ ኢትዮጵያዊ ሕይወት ያጠፉ አውሬዎች ዛሬ በውዳሴ ሲቆላመጡ (ኢሱ ኢሱ ሲባሉ) ለማድመጥ ምጸቱ ፈሶብናል ።

ስንቱ ሺህ ወጣት ኢትዮጵያዊ ውድና ለጋ ሕይወቱን የገበረው፤ግብረ ስየልን የተቀበለውና የተሰቃየው በዓላማ እንጂ፤ ለኢትዮጵያና ለጭቁኑ ሕዝብ እንጂ ከሆኑ ጋር በፊደል አጠቃቀም ጠግጮ እንዳልነበር ብንነግራቸውም፤ውዛደር ላባደር በሚል ለጠብ የሚያደርስ ልዩነት አለመከሰቱን ብንነግራቸውም ፡ ዋለልኝ ስለ ብሔር ጥያቄ ከመጻፉ ከዓመታት በፊት ቢያንስ የኢርትራ ጀብሃ ድርጅት ተቋቁሙ እንደነበርና ብዙ አመጾችም መከሰታቸውን ብናስረዳቸውም፤ሀቅኛ ታሪክ ብንነግራቸውም አሻፈረን ብለው የአገዛዞችን ውሸት ማስተጋባቱን የመረጡ የፖለቲካ ዕውሮች እስካዛሬም አሉ ።አውቅኩ ባይ ሹምም ከዚህ መንጋ ተደባልቆ አወቅሸ አወቅሸ ቢሏት ንግግሩን ያሰማው በዚሁ ወያኔያዊና የሸት መንፈስ መሆኑን ታዝብናል ።ዋለለኝና የዚያ ትውልድ ጀግኖች ቢያንስ ለዓላማቸው የተሰውና ውድ ሕይወታቸውን ለሀገር የሰጡ ነበሩ ። መኩሪያዎች ።ዛሬ ይህን ለማለት አፍ ሞልተው መናገር የማይችሉ ብዙዎች በመሆናቸው ያንን ትውልድ በማውገዝ ላይ አተኩረው ይገኛሉ ።ማፈሪያዎች ። የነበረንና የሰለቸንን ውሸት --ያውም ሳያድሱ-ደግመው ደጋግመው እንደ ሞኝ ልቅሶ የሚያሰሙን ያለውን ሁኔታ ለማደብዘዝና ዕይታችንን ለማንሸዋረር መሆኑን መሳት የለብንም ።የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጠላቶችን እንደ ወዳጅ አቅርበው ውሉን ሊያስቱን ሲጥሩም ይኸው ማየት ተገደናል ። መሬታችን --ቋራ ለሱዳን፤ ለገሃር ለኤሚሬትስ ወዘተ ተቸብችቧል ። የሀገርሉ ዓላዊነት ተደፍር፤ አንድንት ተሸርሽሮ ነግ ምን ሊመጣ በሚል ስጋት እንድንገባም እየገፉን ናቸው ።ይህን ያፈጠጠ ሀቅ ስንነግራቸው አልሰማ ብለው፤ከሀቅ ርቀው ለሀገር የተሰዉትን አውግዘው ኢትዮጵያን ለጥፋት እየዳረጓት ነው ። የተያዘው ጎዳና ለወያኔ እንጂ ለሕዝብ ከቶም እንደማይጠቅም፤ሕዝብ የመረጠው ሳይሆን አረቦችና አሜሪካ የጫኑብን መሆኑን ሁሉም እያወቀ ስለመጣ፤ ዋለልኝን፤ የፈረደበት አማራ ሁሉ፤ኢሕአፓ ፤ያን ጀግና ትውልድ በማጥቃት የገለማን አገዛዝ ለማሻሻጥ፤ ጸረ ኢትዮጵያ የሆነን ሂደት ተወዳጅ ፤ለማድረግ ሲጥሩ መታዘብ ቀጥለናል ። ሀገራችን የሚያስፈልጋትን አንድነትና ዴሞክራሲ ቅድሚያ በመስጠት ስርዓቱ ፈርሶ--መፍረስ መወገድ አለበትምና¨--የሽግግር ሂደት እውን ይሆን ያልነው በአፍራሽነትና ግድየለሽነት ወይም እነሱው በነሱ ብዝሶ በስልጣን

አቋራጭ ጉዞ ሳይሆን ከሀገራችን ቢዚአ የሚሆናትና ስርየት የሚሰጣት ይህ ብቻ በመሆኑ ነው ። በአቅዋማችን ጸንተን፤ ከሕዝብ ጎንም ተሰልፈን ማንኛውንም የባዕድ ሆነ የወያኔ ሴራ ለማክሸፍ አንጥርና ሕዝባዊ አልገዛም ባይነትን ስናንጸባርቅ ታሪካችንንም አቅዋማችንንም ሊያረክሱና ሊበርዙ የተነሱትን ሁሉ መቃወማችን ቀጣይ ሆኗል ። ከምናየው ሽብረብ ተጠቃሚ የሆኑ የማኢያሰሙትን ጫጫታ ብናውቅም--አዛኝ ቅቤ አንጓች የሆኑልንን ጭምር-- በበኩላን ግን ሕዝብ የሚፈልገው ስር ነቀል ለውጥ የሚመጣበት ጎዳና ተዘግቶ ኢትዮጵያን የሚያጠፉ የሚፈነጩበት ዕድል ስለተሰጠ ከግባችን ደረስን ብለን ራሳችንን ማታለሉን ወይም ኦትዮጵያን መካዱን አለመረጥንም ። የትጋለነውና ደም የገበርነው ኦነግ ነን ባይ፤ አዴፓ ኦዴፓ፤ባለሜንጫና የጠባብ መንጋ ሀገራችን ላይ ይጫውት ዘንድ ባላመሆኑ፤ለዴሞክራሲና ለሕዝባዊ መንግሥት በመሆኑ የሚታየው ግርግርና የአምባገነንነት ጉዞ ቅጣይ በዘመኑ አነጋገር ቅንጣትም አልተመቸንም ። የእናት ኢትዮጵያ ህልውና ነውናም ለነሱ ይመቻችሁ ብለን የምንተውላቸው ሊሆን አይችልም ።ትግላችን ተፋፍሞ መቀጠል አለበት ። ሹሙና ይዘቱን የምንቃወመው ኢትዮጵያን ስለምንወድ ብቻ ነው ።

ሸንካላ አቅዋሞችን ልናስተካክል ልናርቅ ስንጥር ብዙ ዓመታት አሳልፈናል ። የሕዝብ መፈክሮች ምላሽ ሳያገኙ ሰንደቃችንን አንጥልም  ስንላቸው አቅዋም የማይቀይሩ ግትሮች ይሉናል ። ወያኔን አምርረን ስንታገል ጸረ ትግሬ ሊሉንም ከጅለዋል ። የሚገርመው ደግሞ አንዳንዶች--ያውም የወያኔ ቅጥረኛ ሆነው የምናቅዋቸው ጸረ አማራም ሊሉን ከጅለዋል ። በዕርቅና ይቅርታ ስም ወነጀለኞችን (እነ መንግሥቱና ፍስሓ ደስታ፤ወያኔና ሽብረተኞችንም ጭምር ) ሊያቅፊ ሲነሱ አሻፈረን ፍትህ ይቅደም ስንልም ቂመኞች ብለውናል ። ከሶማሌና ዚያድ ባሬ ጎን ተሰለፉ የሚለው የደርግ በሬ ወለደ ነው ስንላቸውም አለምንም መረጃና ማጠየቂያ ይህን የደርግ ውሸት ክስ ለዓመታት ደጋግመውብናል ። ሹሙ የሚጠቅመው መስሎት የደርግ ወያኔን ሀሰት ማስተጋባትን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል ።ምንም ጥቅም የለውም ። የአሁኑን ሂደት አሜሪካና አረቦች ያሴሩበት ነው ፤ሹሙን ጌታቸው አልማዝ፤ግደይ ጉደታ፤ መሃመድ ዜይናብ፤ ዘነበች ጫልቱ ሳይሆኑ ያማማቶዎች--አ የመረጡት ነው ። ሀቁ ተወደደን ተጠላም ይህ ሆኖ ባለበት የለም አምላክ/ የላከልን ሹም ነው ሊሉንም ሳያፍሩ ከጀሉ ። እንደ ደጃዝማች ፊታውራሪ  ዶክተር ፕሮፌሰር ታፔላን በጭብርብር ዲግሪ ድረስ የለጠፉ አድርባይ ምሁራን የዓይጥ ምስክሩ ድንቢጥ ሆነው ለሹሙ ጠበቃ ሆነው ውዥንብር ቢያስፋፉም ዋናው ጉዳይ የስር ዓቱ መጠገን ሳይሆን መወገድ ነው የሚለውን አምርረን በመያዛችን ታሪካችንን እየበወዙና በሀሰት እያቀረቡ ሊወነጅሉን ተነስተዋል ። ሀቁ ግን የሚሸፋፈን አይደለም ። አልጥም ያላችውን ሀቅ ምንደጋግመው ሀሰት ሲደጋገም ሀቅ ይመስላል የሚለውን የናዚና ወያኔ ፈሊጥ ለመጻረርም ነው ። የሽግግርን ሂደት ከጥነት ጀምሮ (ከ1966-67) ጀምሮ የምገፋው በቅድሚያ የማንቀርበው ለኢትዮጵያ ችጎርን መፍጥሄ ይሰጣል በሚል ሲሆን ዛሬም ይህን ውሳኝ መፈክር ምናስቀደመው ለሀገር የሚጠቅም ሂደት በመሆኑ ነው ።ወያኔ ኢሕ አዴግን ማደስ መጠገን፤በወያኔ ምርጫ መካፈል የሚሉት ውድቅ አማራጮችንም በፊትም ዛሬም ነገም የማይበጁ መሆናቸውንም አስረግጦ ለማቅረብ ነው ። ወያኔ የግንጣላ መርሃ ግብሩን ሲያቀርብ (በ967 ዓ.ም.) የመጀመሪያ ተቃዋሚዎቹ እኛ ነበርን ።ሻዕቢያ ኤርትር የኢዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ሲል ኢታሪካዊ ነው ብለን የተቃወምነው ኢሕ አፓዎች ነበርን። ይህ ሀቅ ሆኖ ሳለ ለወያኔም ሻዕቢያም ድጋፍን ሰጠ የሚሉን ዛሬ የወያኔ ቅጥረኞች የሆኑ ሃሳዊዎች፤ ታሪክ ማወቅ የተሳናቸው፤ የዛሬውን ስርዓት ሊደግፉ የተነሱ ዋሾዎች ናቸው ።ማንንም ገንጣይ ፤ አንድንም ገንጣይ ያልደገፍን ከመሆናችን በላይ--የሕዝብን መብት ከማወቅ አልፈን--ዛሬም ይህ አቅዋማችን  ጸንቶ የቀጠለ ነው ።በሂደት ማን ምን አቅዋም ይዞ ነበር የሚለው ደግሞ በመረጃ የተደገፈ ዕወት አለን ።ብዙዎች ሲለፍፉ መቀረጻቸውን ረስተው ዛሬ የሚያቀርቡት ግን ከተናገሩት ሌላ ሆኖ ይገኛል ።ለምን ይዋሻል?

ሹሙ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ለቀቅኩ፤ሰላም አሰፈንኩ፤ወዘተ ወዘተ በሚል በባዕዳን ድጋፍ ሀሰትና ውዳሴ ቢያሰራጭም ይህ ሁሉ ህቅ አለመሆኑን ዓመት ሳይሞላ ለመረዳት ችለናል ። ጠበቅ አድርገን ተቃውሞን ያሰማነውና ከመንጋው ግርግርና ጫጫታም ጋር ተቃርነን የተገኘነው ያለው አካሄድ ለኢትዮጵያ ከቶም የማይጠቅም መሆኑን በመረዳታችን ነው ።ይህንንም፤ አልፎም ወያኔ ደርግን ደግፍው ያዙን ልቀቁን ሲሉ የነበሩት ዛሬ የሹሞቹ ድጋፊ ሆነው አዲስ ታሪም ፈብርከው ሲያቀርቡየሀቅ ዋርዲያ በመሆን መኖራችን የምናስቸግራቸው መሆኑ ቅር የሚያሰኝን አይደለም ።ለሀገር ወዳጆች ዋናው ጥያቄ መሆን ያለበት አቅዋማችን ሕዝባዊ ነው፤ሕዝብ ይደግፈዋል ወይስ ይቃወማል የሚለው ነው ። ሕዝብ ከደገፈን ምን ገዶን ?

ሲነገሩ የማይሰሙ ብጹዓን አይደሉም ። ስህተተኞች ናቸው ።ዓይናቸውን ከፍተው የታወሩም መድሃኒት መፈለግ አለባቸው ። ከህቅ የሚጣሉ ይታከሙ ። የሕዝባችን ትግልም ተፋፍሞ ይቀጥል ።

ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕአዴግ ትግላችን ይፋፋም ይቀጥል !!

ኢትዮጵያዊነት ያቸንፋል !!